Istituto Italiano
di Cultura

# Il canto sacro etiopico

# የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዜማ ።

Abba Pietros Hailù
አባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኃይሉ ፡

3

Addis Abeba 1968

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዜማ ።

ሪታና ቤተሰቧ
የግል ቤተ መጻ

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ታሪክ ፡ ከመናገራችን ፡ በፊት ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መቼ ፡ እንደገባ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሲታወሱ ፡ የሚኖሩትንና ፡ የአገሪቱ ፡ ቅርስ ፡ የሆኑትን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎችንና ፡ ኪነ ፡ ጥበቦችን ፡ ተደራርበው ፡ በመፈጸም ፡ ለመደምሰስ ፡ ያበቋቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ምክንያቶች ፡ ባጭሩ ፡ ማብራራት ፡ ይገባል ።

ክብረ ፡ ነገሥትና ፡ ስንክሳር ፡ ስለ፡ ኢትዮጵያውያን፡ ነገሥታት፡ ትውልድ ፡ ሲናገሩ ፡ «ወሕዝበ ፡ ኢትዮጵያሰ ፡ ሀለው ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡ ወእምዝ ፡ መሀሮሙ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ዜና ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእምነቶሙ ፡ [ለነገሥታቲነ] ፡ ኮነ ፡ እምልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፫፻፴፫ ፡ ዓመት» ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ዜና ፡ ነገራቸው ። እምነታቸው ፡ ደግሞ ፡ ከክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፴፫ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ሆነ ፡ እንደሚሉት ፡ ሁሉ ፡ ክርስትና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሁለቱ ፡ ወንድማማች ፡ በቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስና ፡ በኤዴስዮስ ፡ አማካይነት ፡ መሆኑ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይህ ፡ ነገር ፡ በእነ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፡ በታሪክ ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያላቸው ፡ በሶቅራጥስና ፡ በሩፊኖ ፡ የአኵለያ ፡ ተወላጅ ፡ ታሪክ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ሩፊኖ ፡ በጻፈው ፡ በታሪክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በ፩ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በ፱ኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የሚከተለውን ፡ እናነባለን ። በመጀመሪያ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የፊኒቂያ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ መራጵዮስ ፡ የተባለ ፡ ፈላስፋ ፡ ፍሬምናጦስና ፡ ኤዶስዮስ ፡ የተባሉትን ፡ ሁለት ፡ የወንድሙን ፡ ልጆች ፡ ይዞ ፡ ለጕብኘት ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ሄደ ። እዚያ ፡ ባሕሩ ፡ ዳር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ቆይተው ፡ ጕብኝታቸውን ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ለመግባት ፡ ሲነሡ ፡ እቦታው ፡ የነበሩ ፡ አረማውያን ፡ ሰዎች ፡ ፈላስፋው ፡ መራ



www.ethiopianorthodox.org

ጵዮስን ፡ ገደሉት ፤ ሁለቱን ፡ የወንድሙን ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ለአክሱም ፡
ንጉሥ ፡ እንደ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ላኩለት ። ሁለቱ ፡ ወንድማማች ፡
በዕድሜ ፡ ሲያድጉ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በጣም ፡ የተወደዱ ፡ ሆነው ፡
ተገኙ ፤ ከፍ ፡ ላለ ፡ ሥልጣንም ፡ ተሾሙ ። ፍሬምናጦስ ፡ ለቤተ ፡ መንግ
ሥቱ ፡ መዝገብ ፡ ሹም ፡ ሆነ ፡ ኤዶስዮስም ፡ በግምጃ ፡ ቤት ፡ ተሾመ ። እነ
ዚህ ፡ ሁለት ፡ ወንድማማች ፡ የተቀበሉትን ፡ ኀላፊነት ፡ በታላቅ ፡ ታማኝ
ነትና ፡ ትጋት ፡ መፈጸማቸው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ታወቀላቸውና ፡
ንጉሡ ፡ ሲሞት ፡ ንግሥቲቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ አልጋ ፡ ጠባቂዎችና ፡
የአልጋ ፡ ወራሹ ፡ አሳዳጊዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ሾመቻቸው ። ፍሬምና
ጦስና ፡ ኤዶስዮስ ፡ የተሾሙበትን ፡ ሥራ ፡ እንደያዙ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የክር
ርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ሁከት ፡ ለማስገባት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡
እያሉ ፡ ትምህርታቸውን ፡ መስጠት ፡ ጀመሩ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የተከሏት፡
የሃይማኖት ፡ ዛፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ ያላት ፡ ሆነች ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚኰ
ተኵታት ፡ ሰው ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ወንድማ
ሞች ፡ ካገራቸው ፡ ከወጡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኗቸው ፡ ነበርና ፡ አልጋ ፡
ወራሹ ፡ አድጎ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡
አገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡
ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ በርሱና ፡ በወንድሙ ፡ በኤዶስዮስ ፡ አማካይነት ፡ ክር
ስትና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲገባ ፡ ምኞቱ ፡ እንደሆነ ፡ ለመግለጽ ፡
አስቦ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርያ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ከነበረው ፡ ከቅዱስ ፡
አትናቴዎስ ፡ ጋር ፡ ለመገናኘት ፡ ወደ ፡ ግብጻዊ ፡ እስክንድርያ ፡ ሄደ ።
በእነሱ ፡ የተቋቋሙት ፡ አዲሶቹ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ አኗኗር ፡
እንደሚኖሩ ፡ ተረከለት ። እነዚህ ፡ አዲሶች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ያለ ፡ ጳጳስና ፡
ካህናት ፡ የኖሩ ፡ እንደሆነ ፡ ለወደፊቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ችግር ፡ እንደሚገጥ
ማቸው ፡ ጨምሮ ፡ ገለጠለት ። ታላቁ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ በቅዱስ ፡
ፍሬምናጦስ ፡ አማካይነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያቀረበለትን ፡ የነዚህን ፡ የአ
ዲሶቹን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ጉዳይ ፡ በሙሉ ፡ ልቡ ፡ ተቀበ
ለው ፤ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ለተመለሱት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እረኛና ፡ አባት ፡
ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ደግሞ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተረዳው ። ሩፊኖስም ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ከፍሬምና
ጦስ ፡ ወንድም ፡ ከኤዶስዮስ ፡ አፍ ፡ የሰማነው ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ታሪኩን ፡
ይዘጋል ።

ከብዙ ፡ ምርመራ ፡ በኋላ ፡ በታተመው ፡ በመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘኢት
ዮጵያ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ ፲፮ኛው ፡ ገጽ ፡ «ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ከአት
ናቴዎስ ፡ ፭ ፡ ዓመት ፡ አዲሳትን ፡ ተምሮ ፡ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ ይዞልን ፡
መጣ ፡» የሚለው ፡ አነጋገር ፡ የሩፊኖስን ፡ ታሪክ ፡ ይደግፋል ።

በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ተብሎ ፡
የሚጠራው ፡ የቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ስብከት ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ተቋ



ርጦ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በ፭ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በአልአሜዳ ፡ ዘመነ ፡ መን
ግሥት ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ ሮማውያን ፡ መነኰሳት ፡ የተባሉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ፡
መግባታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ። ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡
እንደገቡ ፤ የትውልድ ፡ አገራቸው ፡ የት ፡ እንደሆኑ ፤ ሮማውያን ፡ የተባሉ
በትን ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ያከራከረ ፡
ጉዳይ ፡ ነው ። የእነዚህም ፡ ቅዱሳን ፡ ስም ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፤ አባ ፡ ጰንጠ
ሌዎን ፤ አባ ፡ ገሪማ ፤ አባ ፡ አሌፍ ፤ አባ ፡ ጸሕማ ፤ አባ ፡ አፍጼ ፤ አባ ፡ ሊቃ
ኖስ ፤ አባ ፡ ይምዓታ ፤ አባ ፡ ጉባ ፡ ይባላሉ ። በአፍ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚነገረው
ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብራናዎች ፡ እንደሚታየውም ፡ የክርስቶስን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ሰብከው ፡ የመሠረቱ ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጀመሪያ ፡ ገዳ
ማትን ፡ ያቋቋሙ ፡ እነዚህ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ በሕዝቡ ፡
ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ክብር ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። የታሪክ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደሚና
ገሩት ፡ ከቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ በኋላ ፡ ክርስትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ በይበልጥ ፡
እንዲስፋፋ ፡ ያደረጉ ፡ እነዚህ ፡ መነኰሳት ፡ ናቸው ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍ
ትንም ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ የተረጐሙት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ዜማች
ንም ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ውጤት ፡ ያገኘው ፡ በእነዚህ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ ሳይሆን ፡
አይቀርም ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

በ፲ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ዮዲት ፡ የምትባል ፡
ሴት ፡ ነግሣ ፡ ነበረች ። ይህች ፡ ሴት ፡ ፵ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ በቆየው ፡
የጭካኔ ፡ አገዛዟ ፡ በየጊዜው ፡ ጦርነት ፡ እያነሣችና ፡ እየዘረፈች ፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ በዕውቀት ፡ አብቦ ፡ በሥልጣኔም ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡
የነበረውን ፡ ታላቁን ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ደመሰሰችው ። ይህቺ ፡
የክርስቲያን ፡ ዋና ፡ ጠላት ፡ የነበረች ፡ ሴት ፡ ከፈጸመቻቸው ፡ አሳዛኝ ፡
ድርጊቶች ፡ አንዱ ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፬ኛው፡
ክፍለ ፡ ዘመን ፡ በታላቅ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ተሠርቶ ፡ የነበረውን ፡ የአክሱም ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ማቃጠል ፡ ነው ። ከቃጠሎ ፡ ብዛት ፡ የተነሣም ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያኑ ፡ አጊጦበት ፡ የነበረው ፡ ወርቅ ፡ ቀልጦ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡
ይፈስ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በየገዳማቱ ፡
የነበሩት ፡ እንደተቃጠሉ ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ክቡር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡
የነበሩት ፡ መጻሕፍትም ፡ ተቃጥለው ፡ ቀሩ ።

በኢትዮጵያ ፡ ዕውቀት ፡ አብቦ ፡ በታየበት ፡ ጊዜ ፡ አጼ ፡ ልብነ ፡
ድንግል ፡ በነገሡበት ፡ በ፲፮ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ እንደዚሁ ፡ አሕ
መድ ፡ ግራኝ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ተነሣ ። ኢትዮጵያም ፡ ከሁሉ ፡ የባሰ ፡
እጅግ ፡ አሳዛኝ ፡ ወረራ ፡ ገጠማት ። ግራኝ ፡ በቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ተደ
ግፎ ፡ ሙሉ ፡ ትጥቅና ፡ መሣሪያ ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮ
ጵያ ፡ በኩል ፡ እየገፋ ፡ መጥቶ ፡ ምንም ፡ የውጭ ፡ ርዳታ ፡ ያልነበራትን ፡
ኢትዮጵያን ፡ አወደማት ። ይህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አቲላ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምሕ
ረት ፡ በሌለው ፡ ጭካኔ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናትንና ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍትን ፡



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ፡ ገዳማትን ፡ ከመደምሰስ ፡ አልተቆጠበም ። እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የሃይማኖትና ፡ የሊጡርጊያ ፡ (መንፈሳዊ ፡ ሥርዓት ፡) ሕይወት ፡ ስለሆኑና ፡ እንዲሁም ፡ በግራኝ ፡ በተነሣው ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥቱ ፡ ተገን ፡ ስለሆኑ ፡ የጭካኔው ፡ መዓት ፡ በይበልጥ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ወረደ ። በዚህ ፡ ወረራ ፡ ምክንያት ፡ የጠፉት ፡ ብራናዎች ፡ ብዛት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደነበረ ፡ መወሰን ፡ አንችልም ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ብዛታቸው ፡ እጅግ ፡ የላቀ ፡ ለመሆኑ ፡ እርግጠኞች ፡ ነን ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክና ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎች ፡ ጥናት ፡ ሲደረግ ፡ የሚፈጠረው ፡ ችግር ፡ አሁን ፡ በተገለጡት ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ የተነሣ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። ምክንያቱም ፡ በታሪክ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የነበራቸው ፡ የጥንት ፡ ጽሑፎች ፡ በመቃጠላቸው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መቼ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሲፈለግ ፡ ስለሚያዳግት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያትም ፡ አሁን ፡ ስለምንነጋገርበት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዜማ ፡ ታሪክ ፡ መግለጫ ፡ ለመስጠት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ።

∴ ∴ ∴

የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እፊታቸው ፡ አስቀምጠው ፡ የሚጠቀሙባቸው ፡ የጥንት ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ሊያገኙ ፡ ስለማይችሉ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ታሪኩን ፡ ከሥሩ ፡ አንስተው ፡ በሰፊው ፡ አጣርተው ፡ ሊጽፉ ፡ አልቻሉም ። ሆኖም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜማ ፡ ታሪክ ፡ ከሥሩ ፡ በድርሰት ፡ ዓይነት ፡ ያቋቋመው ፡ ቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ መሆኑ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ያሬድ ፡ በልጅነቱ ፡ የአባ ፡ ጌዴዎን ፡ ቆይቶም ፡ የአባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ ተማሪ ፡ ነበር ። ያሬድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜማ ፡ ያመነጨና ፡ እንዲስፋፋም ፡ ያደረገ ፡ እሱ ፡ ስለሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ፈጣሪ ፡ ይባላል ። ስለ ፡ ትውልዱ ፡ በሰፊው ፡ ባይታወቅም ፡ የአክሱም ፡ ተወላጅ ፡ መሆኑና ፡ ትውልዱ ፡ የካህናት ፡ የእነ ፡ አባ ፡ ጌዴዎን ፡ ወገን ፡ መሆኑ ፡ ይነገራል ። ክብረ ፡ ነገሥት ፡ «ወካሌብ ፡ ወለዶ ፡ ለገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘበመዋዕሊሁ ፡ ደረሰ ፡ ያሬድ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር» ፡ በዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ያሬድ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ፡ የደረሰበት ፡ ካሌብ ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ወለደ ፡ እንደሚል ፡ በፈረንጅ ፡ አቆጣጠር ፡ በ558 — በ584 በአጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይኖር፡ እንደ፡ ነበር፡ ይነገራል ። ስለ ፡ ሕይወቱና ፡ ስለ ፡ ዜማ ፡ አደራረሱ ፡ የሚተርክ ፡ በያይነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታሪክ ፡ አለ ። የያሬድ ፡ ሥራ ፡ ሊስፋፋ ፡ የቻለው ፡ ደራሲው ፡ በአጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይኖር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ አጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ በጣም ፡ ዜማ ፡ አፍቃሪና ፡ ያሬድ ፡ ያዘጋጃቸው ፡ ለነበሩት ፡ ዜማዎችም ፡ ንጉሡ ፡ የሥራ ፡ ተካፋይ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ተመራማሪ ፡ ሰው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ የተቀበለችው ፡ በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መሆኑ ፡ በታሪክ ፡ ከተረጋገጠ ፡



ያሬድ ፡ ዜማ ፡ መድረስ ፡ የጀመረው ፡ ደግሞ ፡ በ፮ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሬድ ፡ እስከመጣበት ፡ ድረስ ፡ ስትቀድስ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ዜማ ፡ ሥርዓተ ፡ ቅዳሴንና ፡ መዝሙረ ፡ ማሕሌትን ፡ ትፈጽም ፡ ኖሮዋል? ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ። ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ አቅርቦ ፡ ወይም ፡ አፈ ፡ ታሪክን ፡ ጠቅሶ ፡ መመለስ ፡ ባይቻልም ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ፫፻ ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ በግሪክ ፡ ነጋዴዎች ፡ አማካይነት ፡ የግሪክ ፡ የትምህርት ፡ ዕውቀት ፡ (Cultura) ኢትዮጵያ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፤ ይህንንም ፡ የሚያረጋግጠው ፡ በ፬ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ የአክሱም ፡ ንጉሥ ፡ በጊዜው ፡ ያገኘው ፡ ድል ፡ ለሚመጡ ፡ ትውልዶች ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ባቆመው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ በግሪክና ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ቀርጾ ፡ የተወው ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ የሚኖረው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ ጋራ ፡ በንግድ ፡ ተገናኝታ ፡ ነበርና ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ በመዲተራኒዮ ፡ አጠገብ ፡ ባሉ ፡ አገሮች ፡ ይነገር ፡ እንደነበር ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይነገር ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። በኢትዮጵያ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖትን ፡ ያስገባው ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬምናጦስም ፡ የግሪክ ፡ ትምህርት ፡ ዕውቀት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይልቁንም ፡ በአዱሊስ ፡ (ዛሬ ፡ ዙላ ፡ በሚባለው ፡) በደንብ ፡ ተመሥርቶ ፡ አገኘው ። እርሱ ፡ ራሱም ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ይሰብክ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ እንችላለን ።

ስለዚህ ፡ ከያሬድ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በግሪክ ፡ ዜማ ፡ ይዜም ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ወደ ፡ ንግግራችን ፡ መነሻ ፡ መለስ ፡ ብንል ፡ ያሬድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዜማ ፡ አሻሻለ ፡ ሳይሆን ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍትን ፡ ደረሰ ፡ እንላለን ። ከእነዚህም ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠውና ፡ ገናና ፡ ስም ፡ ያለው ፡ ድጓ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ የዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ድጓ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኋላ ፡ የመጡ ፡ ሊቃውንት ፡ ሲገለብጡት ፡ አንዳንድ ፡ ሥርዋጽ ፡ ቢያገቡበት ፡ መሠረቱ ፡ የያሬድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዓመቱ ፡ ሙሉ ፡ የሚያገለግል ፡ ሆኖ ፡ በአራቱ ፡ ክፍሎች ፡ በሐጋይ ፡ በጸደይ ፡ በክረምት ፡ በመጸው ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ውስጥ ፡ በዓመት ፡ ሙሉ ፡ ያሉ ፡ በዓላት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ የእናታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፤ የመላእክት ፤ የሐዋርያት ፤ የሰማዕታት ፤ የጻድቃን ፡ ባጭሩ ፡ ስንክሳር ፡ የሚቆጥራቸው ፡ በዓመት ፡ ያሉ ፡ በዓላትን ፡ ይዞ ፡ ያለ ፡ ነው ። ድጓ ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ሌሎችም ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍቶቻችን ፡ ድምጻቸውን ፡ ከሱ ፡ ስለሚወስዱ ፡ ለቀሩትም ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍት ፡ መሠረት ፡ ነው ። ደራሲው ፡ አሳቡና ፡ ቃሉን ፡ የወሰደው ፡ ሁሉ ፡ ከቅዱስ ፡



www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ የዕውቀት ፡ ጽሑፎች ፡ ዋና ፡ ቦታ ፡ ይዘው፡ የነበሩትና ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቁ ፡ የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢት ዮጵያ ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሲጽፉ ፡ ስለ ፡ ያሬድም ፡ ሲናገሩ ፡ «ያሬድ ፡ ብዙ ፡ አዋቂና ፡ ሊቅ ፡ ነበረ ፤ የዜማ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ እየደረሰ ፡ አወጣልን» ፡ ይላሉ ። እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ያሬድ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ያውቅ ፡ እንደነበረ ፡ ይገልጣል ።

አንዳንድ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግን ፡ በ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያላቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ከግብፅና ፡ ከዓረብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቋንቋ ፡ በተገለበጡበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ድጓም ፡ የተደረሰ ፡ ይላሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጽሑፎችና ፡ የሕዝብ ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ የድጓን ፡ ድርሰት ፡ በሙሉ ፡ ለያሬድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ለማንም ፡ ስለማይሰጡት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ የለውም ፤ ይህንኑም ፡ ለማስረዳት ፡ ቀላል ፡ ነው ። ቀደም ፡ ብዬ ፡ እንደገለጥሁት ፡ ያሬድ ፡ የነበረበት ፡ ዘመንና ፡ የቅዱሱ ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ልጅ ፡ አጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ነግሠውበት ፡ የነበረ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ መሆኑ ፡ በክብረ ፡ ነገሥት ፡ ተረጋግጧልና ፡ በ፲፫ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ሊሆን ፡ አይቻልም ። ያሬድ ፡ ድጓን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ብዙዎች ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍትንም ፡ ደርሷል ። እነርሱም ፡ ጾመ ፡ ድጓ ፡ በሑጸም ፡ ጊዜና ፡ በሕማማት ፡ የሚዜም ፤ ምዕራፍ ፤ በእሑድ ፡ በዐበይት ፡ በዓላት ፤ በዐቢይ ፡ ጾም ፡ ጊዜ ፡ ዘወትርም ፡ የሚደረስ ፡ ጸሎት ፤ ዝማሬ ፡ ከቊርባን ፡ በኋላ ፡ የሚዜም ፤ መዋሥዕት ፡ ለሙታን ፡ የሚሆን ፡ የዓመት ፡ ድርሰት ፡ ያለው ፡ ዜማ ፡ ናቸው ። እነዚህንም ፡ ሊቁ ፡ ደራሲ ፡ አብዛኛውን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትውፊት ፡ የወሰዳቸው ፡ ናቸው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። የድጓ ፡ ድርሰት ፡ መጽሐፉ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ነው ። ከትልቅነቱ ፡ የተነሣ ፡ የመገልበጡ ፡ ሥራ ፡ አድካሚ ፡ በመሆኑ ፡ በትልልቅ ፡ አድባራትና ፡ በትልልቅ ፡ አገሮች ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ እጅግም ፡ አይገኝም ። ነገር ፡ ግን ፡ የዓመት ፡ በዓላትና ፡ የሰንበት ፡ የያዘ ፡ ከድጓ ፡ የተቀዳው ፡ በብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚገኝ ፡ «ሰንበተ ፡ አሚን ፡» የተባለ ፡ አነስተኛ፡ መጽሐፍ ፡ አለ ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ድጓና ፡ አሁን ፡ ከላይ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ የያሬድ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ሌሎች ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍቶችም ፡ ይገኛሉ ። እነርሱም ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፤ ኪዳን ፤ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፤ ሰዓታት ፡ መልክዕ ፤ ስብሐተ ፡ ፍቁር ፡ ናቸው ። አንዳንዱም፡ በድጓ፡ ውስጥና፡ በዝማሬ ፡ በመሥዋዕት ፡ የሚገኙ ፡ አዋልድ ፡ ዜማ ፡ ተብለው ፡ የሚጠሩ ፡ የቅኔ ፡ ዜማዎች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ በየበዓላቱ ፡ የሚዜሙ ፡ ብዙ ፡ ሰላምታዎችና ፡ ድርሰቶችም ፡ አሉ ። በተለይ ፡ ስለ ፡ ምሥራቅ ፡



ነገር ፡ በእውቀቱ ፡ ስሙ ፡ የታወቀ ፡ ኢኛሲዮ ፡ ጉዲ ፡ ስለ ፡ ሰላምታዎቹና ፡ ድርሰቶቹ ፡ ሲናገር ፡ በአጼ ፡ ዘርአ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ በ1413—1500 የተጻፉ ፡ ናቸው ፡ ይላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኅብረት ፡ የሚዜም ፡ ቢሆን ፡ አዚያሚዎቹ ፡ ድምጻቸው ፡ እንደሚፈቅድላቸው ፡ በስምምነት ፡ ከፍ ፡ ማለት ፡ ወይም ፡ ዝቅ ፡ ማለት ፡ ይችላሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አውሮፓውያን ፡ ደንብ ፡ ባንድ ፡ የኅብረት ፡ ዜማ ፡ ውስጥ ፡ የሁለት ፡ ወይም ፡ የሦስት ፡ ድምጽ ፡ የሚባል ፡ የለውምና ፡ በአዚያሚዎች ፡ ዘንድ ፡ ለማሳጠርና ፡ ለማርዘም ፡ ጥቂት ፡ ነጻነት ፡ አለው ። የምዕራባውያን ፡ ዜማ ፡ ግን ፡ በሙዚቃ ፡ ምልክቶች ፡ ሕግ ፡ በፍጹም ፡ የታሰረ ፡ ስለሆነ ፡ አዚያሚው ፡ በምልክቱ ፡ ትንሽ ፡ ነጻነት ፡ እንኳን ፡ የለውም ።

የዜማችን ፡ ድምጽ ፡ ለማይገባው ፡ ይልቁንም ፡ የሙዚቃ ፡ ድምጽ ፡ በመስማት ፡ ላደገ ፡ ላንድ ፡ ምዕራባዊ ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የኃዘን ፡ ድምጽ ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ የተዘባረቀ ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡ የሌለው ፡ ዜማ ፡ መስሎ ፡ ይሰማዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በደንብ ፡ የዜማ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ሲያዜሙት ፡ ብዙ ፡ ያማረና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሆኖ ፡ ያገኙታል ። ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የዜማችን ፡ ምልክት ፡ ከምዕራባዊ ፡ የዜማ ፡ ምልክት ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ የተራራቀ ፡ መሆኑን ፡ ማስተዋል ፡ ይገባል ። የኛ ፡ ምልክቶች ፡ በፊደላትና ፡ በሰው ፡ ስምምነት ፡ ምልክቶች ፡ እንዲሆኑ ፡ ተወስነው ፡ የቆሙ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ አስቀድመን ፡ ታሪካቸውን ፡ እንስማ ። የኢትዮጵያ ፡ የዜማ ፡ ምልክት ፡ በያሬድ ፡ ነው ፡ የተጀመረው ፡ የሚል ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ አይጠፋም ። እንደ ፡ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ የተጀመረው ፡ አጼ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ በ፲፭፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሁለት ፡ መነኰሳት ፡ ነው ። ይህንን ፡ ነገር ፡ ለማስረዳት ፡ በታሪከ ፡ ነገሥት ፡ «አጼ ፡ ገላውዴዎስ ፡ በነገሡበት ፡ ጊዜ ፡ አዛዥ ፡ ጌራና ፡ አዛዥ ፡ ራጉኤል ፡ የተባሉ ፡ መነኰሳት ፡ በጣም ፡ ዜማ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ስለነበሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜማ ፡ ምልክትን ፡ አወጡ ፡» ይላል ። ዜማችን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አለ ፡ ምልክት ፡ ይዜም ፡ እንደነበረ ፡ አያጠራጥርም ። በኢትዮጵያ ፡ ገዳማትና ፡ በአውሮጳ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገኙ ፡ የዜማ ፡ ብራናዎችና ፡ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ የመረመርናቸው ፡ በቫቲካን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገኙ ፡ የቅዳሴ ፡ ብራናዎች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውን ፡ ማስረጃ ፡ ያረጋግጡልናል ። ከ፲፭፻ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ያሉ ፡ የዜማ ፡ መጻሕፍቶች ፡ አለ ፡ ምልክት ፡ ይገኛሉ ፤ ከ፲፮፻ ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ግን ፡ ከነ ፡ ምልክታቸው ፡ ይገኛሉ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በዜማ ፡ ምልክት ፡ ማድረግ ፡ የተጀመረው ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ያስደፍራል ።

አዛዥ ፡ ጌራና ፡ አዛዥ ፡ ራጉኤል ፡ ፊደላዊና ፡ ፊደላት ፡ የሌላቸውን ፡ ምልክቶች ፡ ሲጀምሩ ፡ የምልክቶቹ ፡ ቊጥር ፡ የተወሰነ ፡ አድርገውት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነበር ። በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ የመጡ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ በዜማ ፡ ያልበሰሉ ፡ አዚያሚዎች ፡ የፊደል ፡ ምልክትን ፡ እንደሚመስላቸው ፡ አድርገው ፡ ተመሳሳዮች ፡ የሆኑ ፡ ፊደላት ፡ ምልክትን ፡ እየለዋወጡ ፡ አንዱን ፡ ቃል ፡ በሌለው ፡ ቃል ፡ እያመለከቱ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አሁን ፡ የዜማችን ፡ ምልክቶች ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ስለበዙ ፡ ቊጥራቸውን ፡ ለመወሰን ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኗል ። ዜማችንን ፡ ለማጥናት ፡ የሚፈልጉ ፡ አዲሶች ፡ ተማሪዎች ፡ መሠረታዊ ፡ የሆኑትን ፡ ዜማዎች ፡ ካላወቁ ፡ በዜማ ፡ ጥናት ፡ መራመድ ፡ ያዳግታቸዋል ። እነርሱም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ መስተጋብዕ ፡ አርባዕት ፡ አርያም ፡ ሠለስት ፡ ምዕራፍ ፡ የሚባሉ ፡ የቃል ፡ ትምህርት ፡ የዜማ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለሆኑ ፡ ጀማሪ ፡ ተማሪዎች ፡ የሆኑ ፡ እነዚህን ፡ ካወቁ ፡ በውስጣቸው ፡ ያሉትን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የዜማ ፡ ምልክቶች ፡ ለመማርና ፡ ለማጥናት ፡ ገርና ፡ ቀላል ፡ ይሆንላቸዋል ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ምልክቶች ፡ ፩ኛ ፡ ፊደላዊ ፤ ፪ኛ ፡ ፊደልነት ፡ የሌላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ አቀማመጣቸው ፡ በየፊደሉ ፡ ራስጌ ፡ በረቂቅ ፡ አጻጻፍ ፡ ሆኖ ፤ አንዳንድ ፡ ምልክት ፡ የመጀመሪያንና ፡ የመጨረሻውን ፡ አንዳንዱም ፡ ምልክት ፡ የመዠመሪያውን ፡ ብቻ ፡ አንዳንዱም ፡ የመካከለኛውን ፡ ብቻ ፡ አንዳንዱም ፡ ደግሞ ፡ የመጨረሻውን ፡ ብቻ ፡ የሚያመለክት ፡ እየሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ዓይነት ፡ ምልክቶች ፡ እየተቀላቀሉ ፡ ይገባሉ ።

ፊደልነት ፡ የሌላቸው ፡ ምልክቶች ፡ ቊጥራቸው ፡ ፯ ፡ ሲሆን ፡ ስማቸውም ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱ ፡ ናቸው ።

ሀ) ደረት ፡
ለ) ድፋት ፡
ሐ) ቊርጥ ፡
መ) ቊረት ፡
ሠ) ይዘት ፡
ረ) ርክረካ ፡
ሰ) ሂድ ፡



ስለስማቸው ፡ አዚያሚዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አዘያየም ፡ ስለሚያዜሙዋቸው ፡ እንደየሥራቸው ፡ ሠየሙዋቸው ።

በኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የድምጽ ፡ ልዩነት ፡ የፈጠረው ፡ ያሬድ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጽኑ ፡ አፍአዊ ፡ ታሪክ ፡ አለ ። በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ በቁም ፡ ዜማና ፡ ከመሣሪያ ፡ ጋር ፡ በሚዜም ፡ ዜማ ፡ ይከፈላል ። ቁም ፡ ዜማ ፡ ደግሞ ፡ እንደገና ፡ ግዕዝ ፤ አራራይ ፡ ዕዝል ፡ ተብሎ ፡ በ፫ ፡ ይከፈላል ። የሚለያዩበትም ፡ በድምጻቸው ፡ ወይም ፡ በአዛዜማቸው ፡ ነው ። በግዕዝና ፡ በአራራይ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡



እጅግ ፡ ስላልሆነ ፡ በዜማ ፡ ያልገፋ ፡ ሰው ፡ በቀላሉ ፡ ሊለየው ፡ አይችልም። ሆኖም ፡ የግዕዝ ፡ ድምጽ ፡ አጭር ፡ ሲሆን ፡ የአራራይ ፡ ከሱ ፡ ረዘም ፡ ያለ ፡ በጣም ፡ ያማረ ፡ ነው ። ዕዝል ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ርክረካ ፡ ያለው ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ዜማውም ፡ ኃዘንና፡ ርኅራኄን፡ የሚያነሳሳ፡ ነው ። ኢትዮጵያዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሦስቱንም ፡ ዜማዎች ፡ የምታዜምባቸው ፡ ስትሆን ፡ የሚከተሉት ፡ ደንቦች ፡ አሏት ።

ሀ) ከመስከረም ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ኅዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዕዝል ።
ለ) ከኅዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ስብከት ፡ ግዕዝ ።
ሐ) ከስብከት ፡ እስከ ፡ ቅበላ ፡ ዕዝል ።
መ) ከቅበላ ፡ እስከ ፡ ትንሣኤ ፡ ግዕዝ ።
ሠ) ከትንሣኤ ፡ እስከ ፡ ሰኔ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ዕዝል ።
ረ) ከሰኔ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ ፳፭ ፡ ግዕዝ ፡ ይዜማል ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ማስተዋል ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነገር ፡ አለ ። ዜማውን ፡ በሁለት ፡ ብቻ ፡ የከፈልነው ፡ ግዕዝና ፡ አራራይ ፡ ባንድ ፡ ዜማ ፡ ውስጥ ፡ አብረው ፡ ስለሚገኙና ፡ ጊዜያቸውም ፡ አንድ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በዓውደ ፡ ዓመት ፡ ቀናት ፡ የሚዜመው ፡ ግን ፡ በዕዝል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ዜማ ፡ ከእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ዓይነቶች ፡ የትኛው ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ የሚቻለው ፡ በምልክቶቹ ፡ ነው ። በጥቁር ፡ ቀለም ፡ የሚመለከቱ ፡ ግዕዝና ፡ አራራይ ፡ ናቸው ። በቀይ ፡ ቀለም ፡ የሚመለከቱ ፡ ግን ፡ እዝል ፡ ናቸው ።

በዜማ ፡ መሣሪያ ፡ እየታጀቡ ፡ የሚዜሙ ፡ ዜማዎች ፤ ዝማሜ ፤ መረግድ ፤ ወረብ ፤ ጽፍዓት ፡ ይባላሉ ።

ሀ) ዝማሜ ፡ የተባለው ፡ ዜማ ፡ ለዚሁ ፡ ተብሎ ፡ የተበጀው ፡ ዘንግ ፡ (መቋሚያ) ፡ ይዘው ፡ መዘምራን ፡ በመስቀለኛ ፡ ወይንም ፡ ባራት ፡ ማዕዘን ፡ ላይ ፡ በማወዛወዝ ፡ አማትበው ፡ ሲያበቁ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እያሳረፉ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡ ዜማ ፡ ነው ።

ለ) መረግድ ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ ተብሎ ፡ በሁለት ፡ ይከፈላል ። ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ የተባለበትም ፡ ምክንያት ፡ በዜማው ፡ ማጠርና ፡ መርዘም ፡ ነው ። ሁለቱም ፡ ዓይነቶች ፡ በከበሮና ፡ በጸናጽል ፡ ታጅበው ፡ ይዜማሉ ።

ሐ) ወረብ ፡ የተባለው ፡ በከበሮ ፡ ወይንም ፡ በጸናጽል ፡ በጭብጨባ ፡ ይዜማል ።

መ) ጽፍዓት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በከበሮና ፡ በጭብጨባም ፡ ተሸኝ ፡ ቢሆን ፡ ዜማው ፡ ፈጣን ፡ ወይም ፡ ቀልጣፋ ፡ ነው ። ሽብሸባውም ፡ የጽፍዓት ፡ ክፍል ፡ ነው ። አንድ ፡ ቁም ፡ ዜማ ፡ በእነዚህ ፡ አራት ፡ ዓይነት ፡ ዜማዎች ፡ የሚዜም ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

የቅኔ ፡ ዜማ ፡ ባጭሩ ። የቅኔ ፡ አዜያየም ፡ በሐረግና ፡ በቤት ፡ የተወሰነ ፤ እስካሁን ፡ ከተናገርናቸው ፡ ዜማዎች ፡ በፍጹም ፡ የተለየ ፡ ነው። ቅኔ ፡ በዓውደ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ በሰንበትና ፡ በአንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜዎች ፡ ይቀኛል ። ቅኔ ፡ ከሁለት ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ቤት ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ፤ በጠቅላላውም ፡ አሥራ ፡ ሦስት ፡ የቅኔ ፡ ዓይነቶች ፡ አሉ ። ዓይነቶቹ፡ በአሰካክ ፡ እንደሚለያዩ ፡ ሁሉ ፡ የሚቀኙበት ፡ ጊዜም ፡ ይለያያል ። ቅኔ ፡ ከዜማው ፡ ይልቅ ፡ አሰካኩ ፡ በጣም ፡ አድካሚ ፡ ነው ። የቅኔ ፡ አካሄድ ፡ ነጠላና ፡ ድርብ ፡ ተብሎ ፡ በሁለት ፡ ዓይነቶች ፡ ይከፈላል ። አንደኛው ፡ ዓይነት ፡ ጉልህ ፡ ስለሆነ ፡ ቅኔው ፡ በቀና ፡ መስመር ፡ እንዳለው ፡ ይተረጐማል ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ወርቃ፡ ወርቅ፡ ይሉታል ። ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ በአንጻር ፡ ወይም ፡ በምሳሌ ፡ የሚነገር ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ የሚባለው ፡ ዓይነት ፡ ነው ። ምሥጢሩም ፡ የተሸሸገና ፡ የተደበቀ ፡ ስለሆነ ፡ ፍጹም ፡ ከባድ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ቅኔም ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ይባላል ። ስለምን፡ ቢሉም፡ ባለቅኔው፡ ሰም፡ የተባለውን ፡ ንግግር ፡ አልብሶ ፡ በወርቅ ፡ የተመሰለውን ፡ ምሥጢር ፡ የሚያሰማበት ፡ ድርሰት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሰምና ፡ የወርቅ ፡ መንገድ ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ አደራረግ ፡ ያለውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዜማ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ የዜማ ፡ መሣሪያዎች ፡ ከበሮ ፤ ጸናጽልና ፡ መቋሚያ ፡ ናቸው ። አገልግሎታቸው ፡ ዜማን ፡ መምራት ፡ ወይንም ፡ ለመሸኘት ፡ ነው ። አጠቃቀማቸው ፡ ላልተማረ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሆነ ፡ በዜማ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ የተዛነፈ ፡ እንደሆነ ፡ ዜማው ፡ ይሰበራል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በዜማ ፡ መሣሪያዎች ፡ በመጠቀም ፡ የሚከተለውን ፡ ዜማ ፡ እናሰማችኋለን ፤ «ስምዓኒ ፡ እግዚእ ፡ ጸሎትየ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ወይብጻሕ ፡ ቅድሜከ ፡ ገዐርየ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ወኢትሚጥ ፡ ገጸከ ፡ እምኔየ ። በዕለተ ፡ ምንዳቤየ ፡ አጽምዕ ፡ እዝነከ ፡ ኃቤየ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ እጼውአከ ፡ ፍጡነ ፡ ስምዓኒ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለም ፡ ዓለም ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ዝውእቱ ፡ ብሂል ፡ ንወድሶ ፡ ለዘሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ስቡሕ ፡ ወውዱስ ፡ ዘሣረረ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ በአሐቲ ፡ ቃል” ።

በኢትዮጵያ ፡ በየክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ደብተራ ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራ ፡ ብዙ ፡ የዜማ ፡ አስተማሪ ፡ አለ ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ዜማ ፡ ወዳጅ ፡ ስለሆነ ፡ ቅዳሴ ፡ በሚቀደስበት ፡ ጊዜ ፡ መዘምራኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመጣው ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ተሰጥዎ ፡ የሚባለውን፡ የተመደበለትን ፡ ክፍል ፡ በዜማ ፡ ሲመልስ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ። በኢትዮጵያ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በያውራጃው ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ቢኖሩ ፡ ከፍተኛ ፡ የዜማ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ በበጌምድር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ።



ለመምህራንና ፡ ለዜማ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚሰጡ ፡ ማዕርጎች ፡ ፩ኛ ፡ መሪጌታ ፡ የመዘምራኑ ፡ ሁሉ ፡ መሪ ፤ ፪ኛ ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ በቀኝ ፡ ለሚቆሙ ፡ መዘምራን ፡ አለቃ ፤ ፫ኛ ፤ ግራጌታ ፡ በግራ ፡ ለሚቆሙ ፡ የመዘምራን ፡ አለቃ ፡ ለሆነው ፡ የሚሰጡት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ መምህራኖች፡ የማዕርጋቸው ፡ አጠራር ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ለማዜም ፡ በሚቆሙበት ፡ ጊዜ ፡ የሚይዙት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታ ፡ አላቸው ።

የዜማችን ፡ ስልት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ድረስ ፡ በታላላቅ ፡ መምህራን ፡ አማካይነት ፡ በጥቂቱ ፡ ለወጥ ፡ ቢልም ፡ በመሠረቱ ፡ ከያሬድ ፡ በኋላ ፡ አልተለወጠም ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ። በጥቂቱ ፡ ለወጥ ፡ ያለውም ፡ የዜማ ፡ ስልት ፡ በለወጡት ፡ መምህራን፡ ስም ፡ ይጠራል ። የእነዚህም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።


፩ ፤ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ዜማ ።
፪ ፤ የወንጨሬ ፡ ዜማ ።
፫ ፤ ያጫብር ፡ ዜማ ።
፬ ፤ የቆሜ ፡ ዜማ ።
፭ ፤ የተጉለት ፡ ዜማ ፡ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ፡ ዜማ ፡ ምንም ፡ ከምዕራባዊ ፡ ዜማ ፡ በፍጹም ፡ የተለየ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በዜማ ፡ ትምህርት ፡ በበሰሉ ፡ መዘምራን ፡ ሲዜም ፡ ወይንም ፡ ላንድ ፡ የዜማ ፡ ጣዕም ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ የሚሰጠው፡ደስታና፡ የመንፈስ ፡ መነቃቃት ፡ በቀላሉ ፡ አይገመትም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ የዜማችን ፡ ጣዕም ፡ ላንድ ፡ ምዕራባዊ ፡ አይሰማውም ። እኛም ፡ እንዲሁ ፡ የእነሱን ፡ ዜማ ፡ ጣዕም ፡ ለመረዳት ፡ ችግር ፡ ይሆንብናል ። ከዚህ ፡ የተነሣም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የሚጽፉ ፡ አንዳንድ ፡ ምዕራባውያን ፡ ዜማችንን ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲያወሱ ፡ ጣዕሙ ፡ የማይገባቸው ፡ ስለሆነና ፡ እንዴት ፡ እንደሚያምር ፡ ስለማይሰማቸው ፡ ትክክለኛ ፡ ያልሆነና ፡ መስመር ፡ የለቀቀ ፡ ትችት ፡ ያደርጋሉ ።

በኢትዮጵያ ፡ የቅዳሴ ፡ ሥርዓት ፡ እስከ ፡ ፲፱ኛው ፡ ዘመን ፡ ድረስ፡ በዜማ ፡ እንጂ ፡ በድጋም ፡ አይቀደስም ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ችግሩን ፡ ተመልክታ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ካህናቶችዋን ፡ በድጋም ፡ እንዲቀድሱ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥታቸዋለች ። በሃይማኖት ፡ ከእኛ ፡ የተለዩ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በዜማ ፡ እንጂ ፡ በድጋም ፡ መቀደስ ፡ አልጀመሩም ።




www.ethiopianorthodox.org



ከዚህ ፡ ላይ ፡ የተመለከተ ፡ ዜማ ፡ በግዕዝ ፡ ነው ።

Esempio di canti Ararai con note in lettere e segni convenzionali.



ከዚህ ፡ ላይ ፡ የተመለከተ ፡ በግዕዝና ፡ በአራራይ ፡ እየተወራረስ ፡ የሚዜም ፡ ዜማ ፡ ነው ።

Esempio di canto Ge'ez alternato con Ararai con note come sopra

www.ethiopianorthodox.org

## *Quaderni dell'Istituto Italiano di Cultura*

Istituto Italiano
di Cultura

**THE EUROPEAN ECONOMIC COMMUNITY AND AFRICA**

GIULIO PASCUCCI - RIGHI
Ambasciatore d'Italia

*Lecture delivered at the Italian Cultural Institute, on June 14. 1967.*

Addis Abeba 1967 1

Istituto Italiano
di Cultura

**ASPETTI UMANI DELL'OPERA DI LUIGI PIRANDELLO**

GIOVANNI BATTAGLIA
Direttore dell'Istituto
Italiano di Cultura

*Conferenza tenuta all'Istituto Italiano di Cultura il 19 dicembre 1967.*

Addis Abeba 1967 2

www.ethiopianorthodox.org